የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19[th] Year No. 66
ADDIS ABABA 6[th] September 2013


## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፺፭/፪ሺ፭ ዓ.ም


የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………………ገጽ ፯ሺ፺፯


## CONTENTS

**Regulation No. 295/2013**


Ethiopian Meat and Dairy Industry Development Institute Establishment Council of Ministers Regulation…………………………………………………………………………… Page 7097


**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፭/፪ሺ፭**

**የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) እና (፲፪) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤

፪/ "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤

፫/ "የሥጋና ወተት ምርት" ማለት የእንስሳት ምርትና ተዋፅዖን ያጠቃልላል፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 295/2013**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN MEAT AND DAIRY INDUSTRY DEVELOPMENT INSTITUTE**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 35 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended).

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Meat and Dairy Industry Development Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 295/2013".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "industry" and "manufacturing activity" shall have the meaning given to them under sub-article (11) and (12) of Article 2 of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010;

2/ "production process" means sequence of operation in the performance of manufacturing activity;

3/ "meat and dairy products" means products including livestock products and by-products;


ያንዱ ዋጋ
Unit price 4.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80.001

፬/ "የእንስሳት ምርት" ማለት ሥጋ፣ ወተት፣ ቅቤና አይብ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ምርት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል፤

፭/ "የእንስሳት ተዋፅዖ" ማለት እንደ ቀንድ፣ ሸኮና፣ ደም፣ አጥንትና አንጀት የመሳሰሉ ከእንስሳት እርድ የሚገኙና ተፈላጊነት ያላቸው ተረፈ ምርቶች ሲሆኑ ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ተዋፅዖ ብሎ የሚሰይማቸውን ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ያጠቃልላል፤

፮/ "እንስሳት" ማለት ዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል ፣ ዶሮና ግመል ማለት ሲሆን ኢንስቲትዩቱ እንስሳት ብሎ የሚሰይማቸውን ያጠቃልላል፤

፯/ "ቴክኖሎጂ" ማለት በምርምር፣ በሙከራና በአዲስ የአሠራር ስልት የተገኙና ጥቅም ላይ ሲውሉ የምርት ጥራት፣ ምርታማነትና የአሠራር ቅልጥፍናን የሚጨምሩ የአሠራር ዘዴዎች ናቸው፤

፰/ "ማቀነባበር" ማለት ማንኛውም ምርት በዓይነት፣ በይዘት ወይም በተዛማጅ ሁኔታ ቀድሞ ከነበረው እሴት ለመጨመር የሚደረግ የአሠራር ሂደት ነው፤

፱/ "ሚኒስቴር" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. **መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት ቢሾፍቱ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ለስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን፣ የልማት እመርታ ማምጣት እና ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማብቃት ይሆናል፡፡

4/ "livestock products" means meat, milk, butter and cheese, and includes other products designated by the Institute as livestock products;

5/ "livestock by-products" means by-products such as horn, hoof, blood, bone, instestine and other similar useful by-products of slaughtered animals and includes other by-products designated by the Institute as livestock by-products;

6/ "livestock" means cattle, sheep, goat, chicken and camel and includes other animals designated by the Institute as livestock;

7/ "technology" means methods resulting from research, innovations and new techniques that improve the productivity and quality of meat and dairy products;

8/ "processing" means a mechanism by which the value of a product is increased in terms of type, content or the like;

9/ "Ministry" means the Ministry of Industry;

10/ "person" means natural or juridical person;

11/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Establishment**

1/ The Ethiopian Meat and Dairy Industry Development Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

4. **Head Office**

The Institute shall have its head office in Beshoftu and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. **Objective**

The objective of the Institute shall be to provide all round support to the meat and dairy industry and thereby accelerate technology transfer, achieve transformation and enable the industry to be competitive at international level.

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

፪/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ገበያ ውስጥ እንዲገቡ መደገፍ፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርፀት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ መደገፍ፤

፫/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪን ለማሳደግ የሚያግዙ የገበያ ጥናትን ጨምሮ ሌሎች የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፣ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

፬/ ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤

፭/ ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤ ኢንዱስትሪው የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁም ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል፤

፮/ የእንስሳት ሀብትና ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ ባሉት የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የመረጃ ቋት መመስረት፣ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ በየጊዜው እየተገመገሙ ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፤

፯/ ለእንስሳት ገበያ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ክትትል የማድረግ፤

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ formulate policies, strategies, directives and action plans that assist in the facilitation of the development of meat and dairy industry, and implement same upon approval;

2/ conduct research and development and identify relevant technologies applicable to the development of the meat and dairy industry, transfer these technologies to the industry and support them to enter the market thereafter; and encourage the industry to establish research and development units;

3/ conduct studies and research, including market research, that support the development of the meat and dairy industry; assist the industry to promote their products in the domestic as well as international markets; and work closely with relevant stakeholders in order to implement effective marketing systems in the industry;

4/ collect, analyze and organize technological, market and other data necessary for the development of the meat and dairy industry and disseminate same to users, as may be necessary;

5/ provide consultancy services to meat and dairy industry concerning production process, production planning and quality assurance; establish pilot plants and laboratories to support the industry, provide international-level testing services; encourage the industry to establish laboratories and assist them to get certification so as to make them internationally competitive;

6/ set up a database related to livestock resources and the industry by conducting a survey on investment opportunities, collect, analyze, organize and timely update information necessary for the development of the sector and disseminate same to users, as may be necessary;

7/ follow-up the expansion of infrastructures necessary for livestock market and the availability of facilities such as designated transportation vehicles for livestock and livestock products;

፰/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቋሚ ጥናት ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል ማድረግና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች መፍትሔ መስጠት፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ማካሄድና በንዑስ ዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ መስጠት፤

፱/ በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤

፲/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ በዚህ ረገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋርም በመተባበር የዘርፉን የሰው ኃይል ማብቃት፤

፲፩/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲቻል በቁርኝት መርሐ ግብር የአቅም ግንባታ ማከናወን፤ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሣሣይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

፲፪/ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራት፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፣ በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከርና ኢንዱስትሪዎቹ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖራቸው ማገዝ፤ የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

፲፫/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪውን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለኢንዱስትሪዎቹ ድጋፍ መስጠት፤

፲፬/ ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪዎች እንዲለሙ መደገፍ፤ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤ በተለይም በዘርፉ የተሠማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው መደገፍ፤

8/ prepare and disseminate project profiles that may be helpful in expanding investment in the meat and dairy industry; conduct pilot studies for those investors desiring to engage in the sector; follow up project implementation and provide remedies concerning problems encountered during implementation; promote investment and assist to remove investment bottlenecks in the sector;

9/ advise investors desiring to engage in the meat and dairy industry sector in the selection of technology, negotiation, construction, erection, and commissioning;

10/ provide practical training on technology, technical matters, marketing and management and other tailor-made training that assist the development and competitiveness of the meat and dairy industry sector, and collaborate with the relevant stakeholders to produce qualified manpower in the sector;

11/ build the capacity of the Institute to international standard through twinning programs so as to support the industry effectively; cooperate with national as well as international public and private institutions which have similar objectives and also encourage similar co-operation among private sector institutions;

12/ cooperate with universities on product and human resource development, conduct joint research activities, provide support in building local research capability and in establishing linkages between the industry and the universities; work with technical and vocational training centers to build the human resource of the sector at lower and middle levels;

13/ undertake international benchmarking studies, compile best practices and assist the industry to implement same so as to build their competitiveness globally;

14/ support the development of input industry so as to ensure the regular availability of inputs to the industry in terms of variety, quantity and quality; extend the necessary support and follow up, based on the respective value chain of the industry, starting from raw material up to global market, to ensure effective linkage among the actors, in particular, support the linkage of micro and small enterprises with medium and large industries in terms of production, technology and training;

፲፭/ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሰማራት እንዲነሳሱ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ማበረታታት፣ በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ የሚሰሩ ባለሀብቶችን መደገፍ ፤

፲፮/ በዘርፉ አዳዲስና ተወዳዳሪ ባለሀብቶችን ለመፍጠር ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮግራም መዘርጋትና የኢንኩቤሽን ማዕከላትን ማቋቋም፤

፲፯/ በዘርፉ በጥናትና ምርምር የሚገኙ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤

፲፰/ በድኅረ-ምርት የሚያጋጥሙ የምርት ብክነቶችን ለመቀነስ ድኅረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች፣ ዘመናዊ መጋዘኖች፣ ዘመናዊ ትራንስፖርትና ሌሎች አስፈላጊ የሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤

፲፱/ የሥጋና ወተት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት፤

፳/ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ታዳሽ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀም እና የአካባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤

፳፩/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፳፫/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

8. **የኢንስቲትዩቱ አቋም**

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ አማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

፩/ የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ።

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

15/ promote the development of meat and dairy industry zones to mobilize international and national investors to the sector, and support investors operating in the industry zones;

16/ establish entrepreneurship development program and incubation centers to create new and vibrant entrepreneurs in the sector;

17/ provide support in the acquisition of intellectual property rights and patents for research and technology outputs developed by the sector actors;

18/ promote post harvest technologies, cold chain, modern warehouses, modern transport and other logistics for the sector to reduce post harvest losses;

19/ build the capacity of meat and dairy industry associations so that they play their proper role in the promotion of trade and investment in the sector;

20/ provide support to meat and dairy industry to use renewable energy sources and to operate in environment friendly manner;

21/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the government;

22/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ perform other related activities necessary for the attainment of its objective.

8. **Organization of the Institute**

The Institute shall have:

1/ an Advisory Council (hereinafter the "Council");

2/ a Director General and, as may be necessary , Deputy Director Generals, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. **Members of the Council**

1/ The Chairperson and members of the Council shall be drawn from the appropriate government offices and the private sector and be appointed by the government.

2/ The number of members of the Council shall be determined as required.

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፪. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲፫. የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሠይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፲፬. የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፫/፪ሺ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲፭. ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፫/፪ሺ (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

**፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከነሃሴ ፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፩ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work program and budget of the Institute, and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

**12. Budget of the Institute**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

**13. Books of Account**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

**14. Repealed Regulation**

The Ethiopian Meat and Dairy Technology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No.143/2008 (as amended) is hereby repealed.

**15. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopian Meat and Dairy Technology Institute established under Council of Ministers Regulation No. 143/2008 (as amended) are hereby transferred to the Institute.

**16. Effective Date**

This Regulation shall come into force as of the 9th day of August, 2013.

Done at Addis Ababa, this 6th day of September, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**